


# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## “ቅዱሳን” የተባልነው፥ ለክርስቶስ የተለየን በመሆናችን ነው

### በቃል የሚጠና፡- 1ኛ ጴጥ. 2፥9

*“...በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ....*
*(ፊልጵ. 1፥1)።*

### 1 ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው?

ጳውሎስ በሚጽፋቸው ደብዳቤዎች ሁሉ፥ መግቢው ላይ ጸሐፊው ማን እንደሆነ፥ ለማን እንደተጻፈ ሁልጊዜ ይገልጻል። “ *በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ፥... በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ”* ሲል፥ ደብዳቤው ለፊልጵስዩስ አማኞች የተጻፈ መሆኑ በግልጽ ያሳያል። ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ምዕመናንን *“ቅዱሳን”* ብሎ ለምን ይጠራቸዋል? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። *“ቅዱሳን” ያላቸው፥* “ቅዱሳን” መሆናቸውን ሳያምንበት፥ እነርሱን ደስ ለማሰኘት ብቻ ሲል እያሞጋገሰ የጻፈው አይደለም። *“ቅዱስ”* የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ በትክክል ትርጉሙ ካልገባን፥ “ድካማቸውን እያወቀ ጳውሎስ እንዴት “ቅዱሳን” ብሎ ይጠራቸዋል?” ማለታችን አይቀርም።

*“ቅዱስ”* ማለት ፍጹም የሆነ፥ ምንም ዓይነት እንከን ወይንም ድካም (ኃጢአት) የማይታይበት ማለት አይደለም። ቅዱስ የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ *“ሀጊዮስ”* በዕብራይስጥ ደግሞ *“ካዲሽ”* የሚል ሲሆን፥ ትክክለኛ ትርጉሙ *“ከሌላው የተለየ”* ማለት ነው። ይህን አሳብ የበለጠ ለመረዳት፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረውን አንዳንድ ሁኔታ መመልከት ይጠቅማል። *“ቅዱስ”* ወይንም *“ሀጊዮስ”* ተብለው የሚጠሩት እንዴት ዓይነት ሰዎች፥ ሁኔታዎችና ቁስ አካሎች ይሆኑ? “ቅዱስ” የሚለውን ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት፥ አንዳንድ ምሳሌዎችን እንጠቅሳለን፥

(ሀ) *በቤተ መቅደስ የሚያገለግለው ካህን፥* ከማንኛውም ሰው የተለየ በመሆኑ፥ “ቅዱስ” ይባላል። ካህኑ *“ቅዱስ”* የተባለበት ምክንያት “የፍጹምነት” ባህሪ ስላለው ሳይሆን፥ በቤተ መቅደስ ውስጥ አምላኩን ለማገልገል ከሌላው ሕዝብ *“ተለይቶ የወጣ”* በመሆኑ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ ካህን *“...ለአምላኩ የተቀደሰ ነውና ጋለሞታን ሴት ወይንም የረከሰችውን አያግባ..”* ይላል (ዘሌዋ. 21፥7)።

(ለ) *የእስራኤል ሕዝብ፥* -- እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር “የተለዩ ሕዝቦች” በመሆናቸው መጽሐፍ ቅዱስ *“ቅዱሳን”* ብሎ ይጠራቸዋል። *“እኔ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና፥ ለእኔም ትሆኑ ዘንድ ከአሕዛብ ለይቻችኋለሁና፥ ቅዱሳን ትሆኑልኛላችሁ”* ይላቸዋል (ዘሌዋ. 20፥26)። እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ ወይንም ቅዱስ ሕዝብ እንዲሆኑ እግዚአብሔር ራሱ ይምረጣቸው እንጂ፥ እነርሱ ግን “የተቀደሱ” ወይንም የተለዩ መሆናቸውን በተግባር ለማሳየት ፈቃደኞች አልሆኑም። ለደህንነታቸው ምክንያት እንዲሆን ልጁን ወደ ዓለም ሲልከው፥ ከእግዚአብሔር አብ እንደተላከ አምነው በመቀበል ፈንታ፥ በመስቀል ላይ አንጠልጥለው ገደሉት። ዛሬ እስራኤላውያንን ከአሕዛብ የተለዩ ባለ መሆናቸው *“ቅዱስ”* ሕዝቦች ብለን አንጠራቸውም።

(ሐ) *ለእግዚአብሔር የምንሰጠው አሥራት፥ -- “የተቀደሰ ነው”* የምንለው፥ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል የተለየውን ሰው፥ ወይንም የተመረጠውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ስጦታም *“የተቀደሰ”* ወይንም *“የተለየ”* ነው። ለእግዚአብሔር የምንሰጠው *“አሥራት”* ወይንም አንድ አሥረኛው ለእግዚአብሔር የተለየ በመሆኑ *“ቅዱስ”* ነው። መጽሐፍ ቅዱስ *“... ከአሥር አንድ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሆናል”* ይላል (ዘሌዋ. 27፥32)። ለመሆኑ እኔና እናንተ አሥራታችንን ስንሰጥ ለእግዚአብሔር የተቀደሰውን በመስጠት አምልኮታችንን መግለጻችንን ተገንዝበነው ይሆን?

(መ) *ቤተ ክርስቲያን፥* -- እስራኤላውያን *“ቅዱስ”* ሕዝብ፥ ወይንም ለእግዚአብሔር “የተለየ” ሕዝብ ሆነው መኖር ስላቃታቸው፥ የነበራቸውን ሥልጣንና መብታቸውን ወስዶ *“ቅዱስነቱን”* ለቤተ ክርስቲያን እንደሰጠ እናውቃለን። በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን “አዲሷ

እስራኤል"፥ ለእግዚአብሔር *"የተለየች"*፥ ወይንም *"የተቀደሰች"* ሆናለች። እስራኤላውያን ቀድሞ *"ሀጊዮስ"* *"ካዲሽ"* ወይንም *"ቅዱስ"* ይባሉ እንደነበረው ሁሉ፥ አሁን ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ደህንነትን ያገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ *"ቅዱሳን"* ወይንም *"የተለየ ሕዝብ"* ተብለው የመጠራት መብት አግኝተዋል። ክርስቲያኖች *"ቅዱሳን"* ተብለው ሲጠሩ፥ *"ፍጹማን"* የሆኑ፥ ወይንም ምንም ዓይነት ኃጢአት የሌለባቸው ማለት ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔር የተለዩ ሕዝቦች መሆናቸውን መግለጹ ነው። ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ምዕመናን *"...በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ..."* ሲል፥ *"ቅዱስ"* መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ቅዱስ መሆን የቻሉት፥ በራሳቸው ሳይሆን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ በመሆናቸው ብቻ ያገኙት እንደሆነ ይገልጻል። እኔን እናንተን *"ቅዱስ"* ወይንም "የተለየን" እንድንሆን የሚያስችለን፥ የራሳችን መልካምነት፥ ወይንም ጥረት ሳይሆን፥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ሲኖረን ብቻ ነው።

## 2 ከዚህ ክፍል የምናገኘው ትምህርት

**1** *"ቅዱሳን" ተብለን መጠራታችን፥ ኃጢአት የለብንም ማለት አይደለም።* ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች *"ቅዱሳ ነን"* ስንል *"ለክርስቶስ ተለይተናል"* ማለታችን ነው እንጂ ፍጹምነታችንን መግለጻችን እንዳልሆነ ማወቅ አለብን።

**2** *"ቅዱስና" ተፈጥሮን መልቀቅ ማለት፥ ወይንም ሌላውን በመምሰል የሚገኝ አይደለም።* "ቅዱስ ነን፤ የተለየን ሕዝብ ነን" ስንል ተፈጥሯዊውን እኛነታችንን ለቀን ሌላ ነገር ሆነናል፥ ወይም እንሆናለን ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ነገር ራሳችንን ሆነን እንድንገኝ እንጂ፥ ያልሆንነውን እንድንሆን አይደለም። አንድ የታወቀ ጸሐፊ በልጅነቱ "ወደፊት ስታድግ ምን መሆን ትፈልጋለህ?" ተብሎ ሲጠየቅ፥ "ለምን ይህን ጥያቄ ጠየቃችሁኝ? ወደፊት ሳድግ መሆን የምፈልገው ሌላ ሰው መሆን ሳይሆን፥ በትልቁ እኔኑ እራሴን መሆን ነው" አላቸው። ራስን ሆኖ ከመገኘት የሚበልጥ ሌላ ምን የተሻለ ነገር ይገኛል? እኔና እናንተ እግዚአብሔር እንደፈጠረን፥ ራሳችንን ሆነን መገኘት አስፈላጊነቱን ስንረዳ፥ ሌላውን ለመምሰል የምናደርገውን ትግል ፈጽሞ እንተዋለን። እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት የምንችለው፥ የሆንነውን ስንሆን እንጂ፥ ያልሆንነውን ለመሆን ስንታገል አይደለም። *"ቅድስናችን"* ሌላውን በመኮረጅ፥ ወይንም ሌላውን በመምሰል የሚገኝ ሳይሆን፥ ቅዱስ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር በመያያዛችን፥ ወይንም በመቀራረባችን ብቻ ነው።

**3** *"ቅድስናችን" ቅዱስ ከሆነው አምላክ በመወለዳችን የሚገኝ ነው።*

***የሕይወት ምሳሌ፦*** አፍሪካውያን እንደ ከብት እየተያዙ ለሽያጭ በሚቀርቡበት ዘመን፥ አንድ ቀን በርከት ያሉ አፍሪካውያን በመርከብ ተጭነው ወደ አሜሪካ ለመሄድ በሰንሰለት ታሥረው በሰልፍ ቆመው፥ ይዟቸው የሚሄደውን መርከብ ሲጠባበቁ ይታዩ ነበር። ያለፍላጎታቸው፥ በግድ ተይዘው ወደባርነት ዓለም መሄዳቸውን ስላወቁ፥ ብዙዎቹ ሲያለቅሱ፥ አንዳንዶቹ ደግሞ ውስጣቸው በሀዘን ተሞልቶ፥ አንገታቸውን አቀርቅረው ይታዩ ነበር። ከነዚህ መካከል አንዱ ብቻ ቀጥ ብሎ፥ ደረቱን አስፍቶ ያለሥጋትና ያለፍርሃት ቆሞ ይታይ ነበር። ባሪያ ከሚሸጡትና ከሚለውጡት ነጋዴዎች መካከል አንዱ፥ የዚህ ሰው ሁኔታ በጣም አስደንቆት፥ "ያ ደረቱን አስፍቶ፥ ቀጥ ብሎ የቆመው ሰው ማን ነው?" ብሎ ጠየቀ። ሌላው ነጋዴ ሲመልስለት፥ "እርሱማ የአገሩ ንጉሥ ልጅ ነው። በሰንሰለት ታሥሮ እንደ ዕቃ ለመሸጥ የቀረበ መሆኑን ቢያውቅም፥ የንጉሥ ልጅ መሆኑን ግን ፈጽሞ መርሳት ያልፈለገ ይመስላል" አለው። አስደናቂ ታሪክ አይደለም?

እኔና እናንተም፥ ምንም ያህል ደስ የማይልና ጨለማ ሕይወት ውስጥ ብንሆን፥ የአሁኑና የወደፊቱ ሕይወታችን መከራና ችግር የበዛበት ቢመስለንም፥ የንጉሦች ንጉሥ የሆነው ጌታ ልጆች መሆናችንን ምንጊዜም መርሳት የለብንም። መከራ ይግፋን፥ ያሰቃየን እንጂ፥ ማንነታችንን እንዲለውጥ ፈጽሞ አንፍቀድለት። እኔና እናንተ "ቅዱስ" ወይንም የተለየን ሕዝቦች መሆን የቻልነው፥ በራሳችን ማንነት ሳይሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመወለዳችን ብቻ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ *"እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚያስደንቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ እግዚአብሔር ለራሱ ያደረጋችሁ ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ"* ይለናል (1 ጴጥ. 2፥9)። *"ቅዱስ"* ሕዝብ መሆናችንን ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ *"ቅዱስ"* ሆነን እንድንኖር እግዚአብሔር ይርዳን።




**አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።**

(ሮሜ 1፥16)




## ሀ የመልእክቱን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት

① *“ቅዱስ”* ማለት ምን ማለት ነው?

② ጳውሎስ *“በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ”* ሲል ምን ማለቱ ነው?

③ በቤተ መቅደስ የሚያገለግለው ካህን *“ቅዱስ”* ለምን ተባለ? (ዘሌዋውያን 21፥7)

④ የእስራኤል ሕዝብ *“ቅዱስ”* ለምን ተባለ? (ዘሌዋ. 20፥26)

⑤ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው አሥራት *“ቅዱስ”* ለምን ተባለ? (ዘሌዋ. 27፥32)

⑥ ቤተ ክርስቲያን *“ቅዱስ”* ለምን ተባለች?

⑦ ክርስቲያኖች *“ቅዱስ”* ተብለው የሚጠሩበት ምክንያት ምንድነው?

⑧ ክርስቲያኖችን ልዩ የሚያደርጋቸው ምንድነው?

⑨ *“ቅድስና”* ተፈጥሮን መልቀቅ ማለት አይደለም ስንል ምን ማለታችን ነው?

⑩ *“ቅድስና”* በራስ ጥረት የሚገኝ አይደለም ስንል ምን ማለታችን ነው?

## ለ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገኘነውን ትምሕርት በግል ሕይወታችን ለመለማመድ…

① ክርስቲያን በመሆኔ ከዓለማውያን የምለይባቸው ነገሮች፥

1.

2.

3.

4.

5.

② ከዓለማውያን ያልተለየሁባቸው ነገሮች፥

1. ______

2. ______

3. ______

4. ______

5. ______

③ ለክርስቶስ “የተለየሁ” እንዳልሆን እንቅፋት የሚሆኑብኝ ነገሮች፥

1. ______

2. ______

3. ______

4. ______

5. ______

④ እነዚህን ድካሞቼን ለማሸነፍ ማድረግ ያለብኝ፥ (መውሰድ) ያለብኝ እርምጃዎች፥


1. ______

2. ______

3. ______


4. ______

5. ______



## “...የመዳንን ራስ ቁር የመንፈስን ሰይፍ ያዙ፥ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።...”

(ኤፌሶን 6፥17)



የትምሕርቱ አዘጋጅ
መለሰ ወጉ

# ስንቅና ትጥቅ

## በኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ተዘጋጅቶ፥ በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ የሚወጣ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።

Ethiopian Outreach Ministry
P.O.Box 2241
York, PA 17405
U.S.A.
Phone/Fax: (717)846-2041
E-Mail: eomusa@aol.com
Internet Address:
www.ethiopianoutreach.com

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድራሻ